# حجابك أيتها المسلمة

# ሙስሊማ ሴት ሆይ! ሒጃብሽን አደራ!

إعداد:
الشيخ عبدالرزاق بن عبدالمحسن البدر

ትርጉም፡ ዩሱፍ አሕመድ

http://t.me/alateriqilhaq

بسم الله الرحمن الرحيم

ምስጋና ለአላህ ይገባው ። በእርሱ እመካለሁ ፣ ወደእርሱ ተጸጽቼ እመለሳለሁ ። ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የሌለ መሆኑን ፣ ሙሐመድ ﷺ የአላህ አገልጋይና መልክተኛ መሆናቸውን ፣ እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ ህዝብን በትክክል የመከሩና የተሰጣቸውን አደራ በአግባቡ የተወጡ መሆናቸውን ፤ መልካም ነገር ኖሮ የተውት ፣ መጥፎ ነገር ኖሮ ያላስጠነቀቁት አንድም ነገር የለም ብየ በእርግጠኝነት እመሰክራለሁ። በእርሳቸው ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ የአላህ ሶላትና ሰላምታ ይስፈን።

አላህን በመፍራት ላይ ነፍሴንም እናንተንም አደራ እላለሁ ፤ አላህን የፈራ ሰው ከክፉ ነገር ይጠበቃል ፤ መልካም ለሆነው ጎዳና አላህ ይመራዋል።

ከዚህ በመቀጠል፣

**የተከበርሽ እህቴ ሆይ!** ጊዜሽን በኢማን ፣ በዒልም ፣ አላህን በመታዘዝና በበጎ ስራ እንዲያሳልፍልሽ ፤ አካልሽን በሂጃብ እንዲሸፍንልሽ አላህን እማጸንልሻለሁ። ይህ ለአንቺ በእርሱ ተጠቃሚ እንድትሆኝ ከአላህ ተስፋ በማድረግ የማቀርብልሽ ስጦታ ነው። እርሱም በማንኛውም ቦታ የምትከበሪበት ፤ ደረጃሽ ከፍ የሚልበት የሒጃብ ጉዳይ ነው። ፡

**የተከበርሽው እህቴ ሆይ!** አላህ ወደትክክለኛው ጎዳና በምመራት በእኛ ላይ የዋለውን ታላቅ ጸጋ በቅድሚያ ልትገነዘቢ ይገባል። ኢስላም ለባሮቹ የወደደው ያለምንም ጉድለት ያሟላው ከእርሱ ውጭ የማይቀበለው የሆነ ዲን ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿إِنَّ الدِّينَ عِندَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ﴾

**"አላህ ዘንድ (የተወደደ) ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው።"** *(አል'ኢምራን ፡ 19)*

﴿وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ الْإِسْلَامِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي الْآخِرَةِ مِنَ الْخَاسِرِينَ﴾

**"ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው።"** *(አል'ኢምራን ፡ 85)*

﴿الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الإِسْلاَمَ دِينًا﴾

**"ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለእናንተ ሞላሁላችሁ፤ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ ፤ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ።"** *(አል'ማኢዳ፡ 3)*

አዎ! ይህ ዲን አላህ በእርሱ ዓቂዳን ፤ ውጫዊና ውስጣዊ ስነ-ምግባርን የሚያሳምርበት ፤ የዱንያን እና የአኼራን ህይወት የሚያስተካክልበት ዲን ነው። እርሱን አጥብቆ ለያዘው ከከንቱ አመለካከት ፣ ከሓጢያት፣ እንዲሁም ከዘቀጠ አመለካከት ፤ ከውርደት ፣ ከጥመት እና ከመንሸራተት የሚያጸዳ ዲን ነው። ኢስላም ታላቅና የተባረከ ዲን ነው። በረከት የሞላበት ለዱንያና ለአኼራው ህይወት ጠቃሚ ፍሬዎችን የሚያስገኝ ዲን ነው።

**የተከበርሽ እህቴ ሆይ!** በዚህ ቦታ አጥብቆ ለያዛቸው ወደትክክለኛው ዲንና ታላቅ ወደሆኑ አቅጣጫዎች የሚመሩ ደረትን ለማስፋት ኢስላምን ለመቀበል የሚያግዙ ጥቅል የሆኑ ዋና ዋና ኢስላማዊ ደንቦችንና ሕጎችን ሁላችንንም በእርሷ እንዲጠቅም አላህን ተስፋ በማድረግ ለማስታወስ እፈልጋለሁ።

**1-ያማረ ፤ ቀጥ ያለና የተሟላ የሆነው ሕግ የአላህ ህግ መሆኑን በእርግጠኛነት ማወቅ፤**

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿أَفَحُكْمَ الْجَاهِلِيَّةِ يَبْغُونَ وَمَنْ أَحْسَنُ مِنَ اللهِ حُكْمًا لِّقَوْمٍ يُوقِنُونَ﴾

**"የማህይምነትን ፍርድ ይፈልጋሉን? ለሚያረጋግጡም ሰዎች ከአላህ ይበልጥ ፍርዱ ያማረ ማን ነው?"** *(አል'ማኢዳ፡ 50)*

﴿أَلَيْسَ اللَّهُ بِأَحْكَمِ الْحَاكِمِينَ﴾

**"አላህ ከፈራጆች ሁሉ ይበልጥ ፈራጅ አይደለምን? (ነው)።"** *(አት'ቲን፡ 8)*

﴿وَهُوَ خَيْرُ الْحَاكِمِينَ﴾

**"እርሱም (አላህ) ከፈራጆች ሁሉ በላጭ ነው።"** *(አል'አዕራፍ፡ 87)*

አንድ ሙስሊም ትዕዛዙ ከአላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - መሆኑን ካረጋገጠ ማንኛውንም ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ይቀበላል።

**2-የተከበርሽ እህቴ ሆይ! ማንኛውም የተሟላ እድልሽ ፣ ክብርሽ የአላህን ህግጋት አጥብቆ ከመያዝ ጋር ቁርኝት እንዳለው እዎቂ። ያንች እድል ወይም ዕጣ አላህን በመታዘዝሽ ወይም ሸሪዓውን በመጠበቅሽ የሚወሰን ይሆናል።**

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከለተውን ተናግሯል፡-

﴿إِن تَجْتَنِبُواْ كَبَآئِرَ مَا تُنْهَوْنَ عَنْهُ نُكَفِّرْ عَنكُمْ سَيِّئَاتِكُمْ وَنُدْخِلْكُم مُّدْخَلاً كَرِيمًا﴾

"ከእርሱ ከተከለከላችሁት ታላላቆቹን (ሃጢያቶች) ብትርቁ (ትናንሾቹን) ሃጢያቶቻችሁን ከእናንተ እናብሳለን። የተከበረንም ስፍራ (ገነትን) እናገባችኋለን።" *(አን ኒሳእ፡ 31)*

﴿قَدْ أَفْلَحَ مَن زَكَّاهَا۞وَقَدْ خَابَ مَن دَسَّاهَا﴾

"(ከሃጢያት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ። የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ።" *(አሽ ሽምስ፡ 9-10)*

**3-የተከበርሽ እህቴ ሆይ! ይህንን አላህ የሰጠሽን ክብር ለመንጠቅና አንቺ ውርደት ላይ የምትወድቂበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚንቀሳቀሱ የኢስላም ጠላቶች መኖራቸውን እዎቂ። ከእነዚህ ግንባር ቀደም ጠላቶች መካከል የአላህና የዲኑ ጠላት የሆነው ሰይጣን ነው።**

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿إِنَّ الشَّيْطَانَ لَكُمْ عَدُوٌّ فَاتَّخِذُوهُ عَدُوًّا إِنَّمَا يَدْعُو حِزْبَهُ لِيَكُونُوا مِنْ أَصْحَابِ السَّعِيرِ﴾

"ሰይጣን ለናንተ ጠላት ነው። ስለዚህ ጠላት አድርጋችሁ ያዙት። ተከታዮቹን የሚጠራው ከእሳት ጓዶች እንዲሆኑ ብቻ ነው።" *(ፋጢር፡ 6)*

የአላህ ጠላቶች ዋና ግብ ሙስሊሟ ሴት በዱንያና በአኼራ ነጃ የምትወጣበትን ስርዓት ለቃ የእነርሱን የተበላሸ ስርዓት እንድትከተል በመሆኑ ማንኛውንም ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባታል።

**4-የተከበርሽ እህቴ ሆይ! ወደመልካም አቅጣጫ መመራት በአላህ መሆኑን ፤ አላህ ያላቀው እርሱ ብቻ የተላቀ ፤ አላህ ያዋረደው ደግሞ እርሱ ብቻ የተዋረደ መሆኑን ልታረጋግጭ ይገባል።**

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَن يُهِنِ اللَّهُ فَمَا لَهُ مِن مُّكْرِمٍ إِنَّ اللَّهَ يَفْعَلُ مَا يَشَاءُ﴾

"አላህ የሚያዋርደውም ሰው ለእርሱ ምንም አክባሪ የለውም። አላህ የሻውን ይሰራልና።" *(ሐጅ፡ 18)*

ስለዚህ ከአላህ ጋር ያለሽን ግንኙነት ማጥበቅና ማጠናከር ፤ ወደአላህ መጠጋት ፤ በዲኑና እና በዱዓ ላይ ጽናት ልታደርጊ ይገባሻል።

ከዱዓዎች ሁሉ ትልቁ፡-

"اللهم أصلح لي ديني الذي هو عصمة أمري ، وأصلح لي دنياي التي فيها معاشي ، وأصلح لي آخرتي التي فيها معادي ، واجعل الحياة زيادة لي في كل خير واجعل الموت راحة لي من كل شر" رواه مسلم

"አላህ ሆይ! የነገሬ ሁሉ መጠበቂያ የሆነውን ሐይማኖቴን አብጅልኝ ፤ መኖሪያየ የሆነችውን ምድረ ዓለም አብጅልኝ ፤ መመለሻየ የሆነችውን የመጨረሻ ዓለም አብጅልኝ ፤ ህይዎቴን ለበጎ ስራ መጨመሪያ አድርግልኝ ፤ ሞቴንም ለእኔ እረፍት አድርግልኝ።" *(ሙስሊም፡ 2720)*

**5-የተከበርሽ እህቴ ሆይ! በአላህ ውዴታ ክብርና ልቅና የምትጎናጸፊበትን መንገድ ትኩረት ልትሰጭ ይገባል።**

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ﴾

"አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው።" *(አል'ሑጁራት፡ 13)*

وفي صحيح البخاري عن أي هريرة رضي الله عنه قال : "قيل للنبي صلى الله عليه وسلم من أكرم الناس ؟ قال أكرمهم أتقاهم"

ቡኻሪ በዘገቡት አቡሁረይራ ﵁ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

ረሡል ﷺ "እጅግ በጣም የተከበረው ሰው ማን ነው?" የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው። "(ከአላህ ዘንዴ) በጣም የተከበረው እጅግ በጣም አላህን ፈሪያቸው ነው።" በማለት ምላሽ ሰጡ። *(ቡኻሪ፡ 3374)*

ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ ልቅናን የፈለገ ሊዳሰስና ሊጨበጥ በማይችል ምናብ ውስጥ ነው ያለው።

**6-የተከበርሽ እህቴ ሆይ! ሴቶችን አስመልክቶም የመጣው የሸሪዓ ህግ ልክ እንደሌላው የዲኑ ህግ ክፍተትና ጉድለት የሌለው የማይበድል መሆኑን በደንብ ጠንቅቀሽ እዎቂ። ይህ የሸሪዓ ህግ ባሮችን ሁሉ ተመልካች ፤ ጥበበኛ እና ከዳኞች ሁሉ በላጭ ከሆነው አላህ የተዘጋጀ ህግ ነው።**

ቁርኣን በሴቶች ላይ በደል ፈጽሟል በማለት ወሰን መተላለፍ ትልቁ ሐጢያት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። እንዲህ አይነት አነጋገር የሚናገሩ ሰዎች ጌታቸውን ተገቢ የሆነ ክብር አላከበሩቱም። አላህን ይፍሩ ፤ የአላህን ህግጋት ክብር ይስጡ።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿ذَٰلِكَ وَمَن يُعَظِّمْ شَعَائِرَ اللَّهِ فَإِنَّهَا مِن تَقْوَى الْقُلُوبِ﴾

"(ነገሩ) ይህ ነው። የአላህንም የሃይማኖት ምልክቶች የሚያከብር ሰው እርሷ ከልቦች የሆነች ጥንቃቄ ናት።" *(ሐጅ፡ 32)*

እነዚህ ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ህግጋቶች በተግባር ሊተገበሩና ሁልጊዜም ልናስታውሳቸው ፤ ቀልባችን እንዲለዝብና የአላህን ህግጋት እንድንቀበል የሚያደርጉ በአጠቃላይ ደረታችንን የሚያሰፉ፣ የሚያረጋጉ፣ ወደአላህ ህግጋት ፊታችንን እንድናዞርና በዱንያም ይሁን በአኼራ እድለኛ እንድንሆን የሚያግዙ መሰረታዊ ታላቅና ጠንካራ ህግጋቶች እና ደንቦች ናቸው።

**የተከበርሽ እህቴ ሆይ!** ዲነል ኢስላም ሴቶች ከወንድ ጋር አይቀላቀሉ ፣ ሂጃብ ይልበሱ በማለት ትዕዛዝ ያስተላለፈው የሴቶችን ክብር ከባለጌዎች ለመከላከል ነው። ሴት በኢስላም ከማንኛውም ቆሻሻ የጠራች እንቁ ነች። በዲኑ ህግና ስርዓት ለመስራት ዕድሉ የገጠመው ምን ትልቅ እድል አጋጠመው! ሁኔታውን ምን አላቀው! በረካውን ምን ከፍ አደረገው!

የአላህን ህግ መከተል ከተለያዩ ጥቅሞች ያግዳል ፤ መጥፎ ነገር ያስከትላል ብሎ መናገር በአላህ ላይ ያለእውቀት መናገር ነው የሚሆነው። ከሓጢያቶች ሁሉ ታላቁ ደግሞ በአላህ ላይ ያለእውቀት መናገር ነው ።

አላህ በተከበረው ቁርዓን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَأَن تَقُولُوا عَلَى اللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ﴾

"በአላህም ላይ የማታውቁትን መናገራችሁን ብቻ ነው በላቸው።" *(አል'አዕራፍ፡ 33)*

**የተከበርሽ እህቴ ሆይ!** ሴቶችን በተመለከተ ከአላህ ኪታብ ባነበብሽ ጊዜ ደረትሽን አስፍተሽ በእርጋታና በጥሞና በማስተንተን አንብቢው። ምክንያቱም የምታነቢው ንግግር አንችን የፈጠረሽ ያስገኘሽ መስሚያ እና መመልከቻ ማለትም አምስቱን የስሜት ህዋሳት የሰጠሽ ጥንክርናን እና ብርታትን ያደረገልሽ ጌታ ንግግር ነው። የአላህ ንግግር እና የፍጡር ንግግር ልዩነቱ ልክ በእርሱ እና በፍጡሮች መካከል ያለውን ልዩነት ማለት ነው።

ከአላህ በመጣው መመሪያ ላይ አደራ በልቦናሽ ውስጥ ያለመቀበል ስሜት እንዳታሳድሪ!

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿فَلاَ وَرَبِّكَ لاَ يُؤْمِنُونَ حَتَّىَ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيْنَهُمْ ثُمَّ لاَ يَجِدُواْ فِي أَنفُسِهِمْ حَرَجًا مِّمَّا قَضَيْتَ وَيُسَلِّمُواْ تَسْلِيمًا﴾

**"በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም ፤ (ምእመን አይሆኑም)።** *(አን' ኒሳእ፡ 65)*

በነብዩ ﷺሐዲሶች መስራት ማለት በቁርኣን መስራት ማለት ነው፡፡

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا﴾

**"መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።"** *(አል' ሐሽር፡ 7)*

ቡኻሪ በዘገቡት ዓብደላህ ብን መስዑድ ﵁ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

*"ወቃሪ ተወቃሪ ፤ የቅንድብን ጸጉር የሚያቀጥኑ ፤ ጥርስ የሚፈነጩ ለውበት የአላህን ፍጥረት ቀያሪ የሆኑትን አላህ ረግሟል፡፡" ከበኒ አሰድ የሆነች ስሟ ኡሙ የእቁብ የምትባል ሴት ዓብደላህ ብን መስዑድ ﵁ የተናገረው ንግግር ደርሷት ወደርሱ እየገሰገሰች መጣች፡፡ "ይህን ይህን ተግባር የሚፈጽምን ሰው የተራገምክ መሆኑ ደርሶኝ ነው ወደአንተ የመጣሁት" አለችው፡፡ "ረሡል ﷺ የረገሙትን በአላህ ኪታብ የሚገኝ የሆነውን የማልረግመው ምን አለኝ?!" በማለት ምላሽ ሰጣት፡፡ "በሁለቱ ሰሌዳ መካከል ያለውን (ቁርኣን) ቀርቻለሁ አንተ የምትለውን በፍጹም አላገኘሁትም፡፡" አለች፡፡ "ብትቀሪው ኖሮ በእርግጥ ታገኝው ነበር፡፡* **"መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።"** *(አል' ሐሽር፡ 7) አላት፡፡ "ቀርቸዋለሁ" አለች ፤ "ታዲያ ከእንዲህ አይነት ተግባር እኮ ከልክሏል!" አላት፡፡ (ቡኻሪ፡ 4886)*

ስለዚህ በትክክለኛ ሐዲሶች መስራት በቁርኣን መስራት ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ከነብዩ ﷺ የመጣውን መያዝ እንዳለብን አላህ በቁርኣን አዟል፡፡

አላህ ለሙእሚን እናቶች የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَاذْكُرْنَ مَا يُتْلَى فِي بُيُوتِكُنَّ مِنْ آيَاتِ اللَّهِ وَالْحِكْمَةِ إِنَّ اللَّهَ كَانَ لَطِيفًا خَبِيرًا﴾

“ከአላህ አንቀጾችና ከጥበቡም ከቤቶቻችሁ የሚነበበውን አስታውሱ ፤ አላህ እዝነቱ ረቂቅ ውስጠ ዐዋቂ ነውና።” *(አል’አህዛብ፡ 34)*

“ሂክማ” በሚል አላህ የጠራው ከነብያችን የተያዘውን ሐዲስ ነው።

**የተከበርሽ እህቴ ሆይ!** እድልሽ የሚወሰነው በጥበብና በተከበሩ አዳቦች የተሞላውን ዲን አጥብቀሽ በመያዝሽ ነው።

የአላህ ፍላጎት ውጫዊ ቁንጅናሽ አይደለም ፤ አላህ የሚፈልገው ውስጥሽ በአላህ ፍራቻ ያማረ እና ያጌጠ መሆኑን ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَلِبَاسُ التَّقْوَىٰ ذَٰلِكَ خَيْرٌ﴾

“አላህን የመፍራትም ልብስ ይህ የተሻለ ነው።” *(አል’አዕራፍ፡ 26)*

﴿وَلَٰكِنَّ اللَّهَ حَبَّبَ إِلَيْكُمُ الْإِيمَانَ وَزَيَّنَهُ فِي قُلُوبِكُمْ﴾

“ግን አላህ እምነትን ወደናንተ አስወደደ። በልቦቻችሁም ውስጥ አጌጠው።” *(አል’ሑጁራት፡ 7)*

**وفي الدعاء المأثور: "اللهم زينا بزينة الإيمان" رواه أحمد**

ኢማም አህመድ በዘገቡት የአላህ መልክተኛ ﷺ የሚከተለውን ዱዓ አድርገዋል፡-

“አላህ ሆይ! በኢማን ውበት አስውበን።” *(አህመድ፡ 18325, ነሳኢይ፡ 1305)*

ኢማን ማለት አላህን መፍራት ፤ የአላህን ሸሪዓ አጥብቆ መያዝ ማለት ነው። በትክክል መዋብ እና እድለኛ መሆን ማለት በዱንያና በአኼራ ከእሳት ቅጣት የምንድንበትን መንገድ አጥብቀን መያዝ ማለት ነው።

**የተከበርሽ እህቴ ሆይ!** በቁርኣን እና በነብዩ ﷺ ሱና ከመጡ ትክክለኛ አቅጣጫዎች ወይም ደንቦች መካከል ከፊሉን ልንገርሽ፡-

## አንደኛ ፡ - ሴቶች በሒጃብ እንዲሸፈኑ አላህ ያዘዘው ትዕዛዝ ነው፤

ሴቶች በሒጃብ እንዲሸፈኑ ትእዛዝ የመጣው እርሷን ከባለጌዎች መጠበቂያ እንዲሆንላት እንጅ ለሌላ አላማ አይደለም። ይህም ከአጅነብዩ ወንዶች አጠቃላይ አካሏን ልትደብቅ ነው።

የሚከተለውን የአላህ ቃል አንብቢ፡-

﴿يَا أَيُّهَا النَّبِيُّ قُل لِّأَزْوَاجِكَ وَبَنَاتِكَ وَنِسَاءِ الْمُؤْمِنِينَ يُدْنِينَ عَلَيْهِنَّ مِن جَلَابِيبِهِنَّ ذَٰلِكَ أَدْنَىٰ أَن يُعْرَفْنَ فَلَا يُؤْذَيْنَ وَكَانَ اللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا﴾

“አንተ ነብዩ ሆይ! ለሚስቶችህ፣ ለሴቶች ልጆችህም ፣ ለምእምናን ሚስቶችም ከመከናነቢያዎቻቸው በላያቸው ላይ እንዲለቁ ንገራቸው። ይህ እንዲታወቁና (በባለጌዎች) እንዳይደፈሩ ከመሆን በጣም የቀረበ ነው። አላህም መሓሪ አዛኝ ነው።” *(አል’አህዛብ፡ 59)*

አላህ ያመኑትን ሰዎች (ሶሃባዎችን) ከነብዩ ﷺ ሚስቶች ጋር ሊተገብሩት የሚገባቸውን ጥንቃቄ ሲያስተምር ደግሞ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَإِذَا سَأَلْتُمُوهُنَّ مَتَاعًا فَاسْأَلُوهُنَّ مِن وَرَاءِ حِجَابٍ ذَٰلِكُمْ أَطْهَرُ لِقُلُوبِكُمْ وَقُلُوبِهِنَّ﴾

“እቃንም (ከመዋስ) በጠየቃችኋቸው ጊዜ ከመጋረጃ ኋላ ሆናችሁ ጠይቋቸው። ይህ ለልቦቻችሁ፤ ለልቦቻቸውም የበለጠ ንጽሕና ነው።” *(አል’አህዛብ፡ 53)*

## ሁለተኛ ፡ - ለመውጣት አስገዳጅ ሀጃ (ጉዳይ) ካልገጠማት በቀር ከቤት አለመውጣት፤

አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَقَرْنَ فِي بُيُوتِكُنَّ وَلَا تَبَرَّجْنَ تَبَرُّجَ الْجَاهِلِيَّةِ الْأُولَىٰ﴾

“በቤቶቻችሁም ውስጥ እርጉ፤ እንደ ፊተኛይቱ መሃይምነት ጊዜ መገለጥም በማጌጥ አትገለጡ።” *(አል’አህዛብ፡ 33)*

የሴት ልጅ ክብር የሚጠበቀው ከቤት ውስጥ በመቀመጧ ነው። ሴት ልጅ ከቤት ከወጣች የአላህ ፍርሃቷና ክብሯ አደጋ ላይ ይወድቃል።

**وفي الحديث أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: "المرأة عورة فإذا خرجت استشرفها الشيطان"**

የአላህ መልክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

“ሴት ልጅ እፍረተ ገላ ናት ፤ (ተጋልጣ) የወጣች ጊዜ ሰይጣን ይቀርባታል።” *(ቲርሚዚይ፡ 1173)*

ሴት ልጅ አደባባይ ከወጣች ሰይጣን መጥፎ ነገሮችን ፤ ብልሹ የሆኑ ባህሪዎችን ለማሰራጨት መቀስቀሻ መሳሪያ ያደርጋታል።

## ሶስተኛ፡ - አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ከወንድ ጋር ካወራች ወንድን በሚስብ ሁኔታ የተለሳሰለሰ ንግግር አለመናገር ፤

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿يَا نِسَاءَ النَّبِيِّ لَسْتُنَّ كَأَحَدٍ مِّنَ النِّسَاءِ إِنِ اتَّقَيْتُنَّ فَلَا تَخْضَعْنَ بِالْقَوْلِ فَيَطْمَعَ الَّذِي فِي قَلْبِهِ مَرَضٌ وَقُلْنَ قَوْلًا مَّعْرُوفًا﴾

“የነብዩ ሴቶች ሆይ! ከሴቶች እንደማናቸው አይደላችሁም ። አላህን ብትፈሩ (ትበልጣላችሁ) ያ በልቡ ውስጥ በሽታ ያለበት እንዳይከጅል በንግግር አትለስልሱም። መልካምንም ንግግር ተናገሩ።” (አል’አህዛብ: 32)

## አራተኛ፡ - አጅነብይ ከሆነ ወንድ ጋር ለብቻዋ አለመቀመጥ፤

وفي الصحيحين عن ابن عباس رضي الله عنهما عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: "لا يخلون رجل بامرأة إلا مع ذي محرم"

በቡኻሪና ሙስሊም ዘገባ ዓብደላህ ብን ዓባስ ﵄ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

“አንድ ወንድ የቅርብ ዝምድና ባለቤት ጋር ካልሆነ በቀር ከሴት ጋር ብቻውን አያግልል።” (ቡኻሪ፡ 5233, ሙስሊም፡ 1341)

## አምስተኛ፡ - ከወንድ ጋር ከመቀላቀል መጠንቀቅ፤

ረሡል ﷺ ከቦታዎች ሁሉ ምርጥና የተከበረ በሆነው መስጅድ “ለሴቶች ከሶፍ መልካሙ የመጨረሻው ሲሆን ክፉው ደግሞ የመጀመሪያው ነው።” ብለዋል። (ሙስሊም፡ 440) ከመስጅድ ውጭ በሚገኙ ቦታዎች መቀላቀል ያለው ጉዳት ደግሞ የከፋ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።

## ስድስተኛ፡ - ከቅርብ ዘመዷ ጋር ካልሆነ በቀር አንዲት ሴት ብቻዋን ከአጅነብይ ጋር ተሳፍራ አለመሄድ።

عن أبي هريرة رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: "لا يحل لا مرأة أن تسافر إلا ومعها ذو محرم منها"

አቡሁረይራ ﵁ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

“ከአንዲት ሴት ልትሳፈር አይገባም ከእርሷ ጋር የቅርብ ዘመድ (መህረም) አብሯት አያለ ቢሆን እንጅ።” (ቡኻሪ፡ 1088, ሙስሊም፡ 1339)

## ሰባተኛ፡ - አንዲት ሴት ከቤት ከወጣች ልብሷን በሽቶ ሳታሻትት ትውጣ።

ففي صحيح مسلم عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: "إذا شهدت إحداهن المسجد فلا تمس طيبا" رواه مسلم ، وروى الإمام أحمد عن النبي صلى الله عليه وسلم قال : "أيما امرأة استعطرت ، فمرت بقوم ليجدوا ريحها فهي زانية"

ሙስሊም በዘገቡት ትክክለኛ ሐዲስ የአላህ መልክተኛ ﷺየሚከተለውን ተናግረዋል፡-

“አንዲት ሴት መስጅድ ከተገኘች ሽቶ አትነካካ።” (ሙስሊም፡ 443)

ኢማም አህመድ በዘገቡት ነብዩ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

“ሽታዋን እንዲያገኙ በሰዎች መካከል ሽቶ ተሳታ ያከፈች ሴት ዝሙተኛ ነች።” (አህመድ፡ 19711, አቡዳውድ፡ 4173, ቲርሚዚይ፡ 2786, ነሳኢይ፡ 5126)

## ስምንተኛ፡ - አንዲት ሴት ለሆነ ጉዳይ ስትወጣ አጅነብይ የሆኑ ወንዶችን ዘወር ዘወር እያለች መመልከት የለባትም፡፡

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው፡-

﴿وَلَا يَضْرِبْنَ بِأَرْجُلِهِنَّ لِيُعْلَمَ مَا يُخْفِينَ مِن زِينَتِهِنَّ﴾

“ከጌጣቸውም የሚሸፍኑት ይታወቅ ዘንድ በእግሮቻቸው አይምቱ።” (አንኑር፡ 31)

## ዘጠነኛ፡ - የአላህን ትዕዛዝ ማክበር አለባት፡፡

አላህ በተከበረው ቁርአን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَقَرْنَ فِي بُيُوتِكُنَّ وَلَا تَبَرَّجْنَ تَبَرُّجَ الْجَاهِلِيَّةِ الْأُولَىٰ وَأَقِمْنَ الصَّلَاةَ وَآتِينَ الزَّكَاةَ وَأَطِعْنَ اللَّهَ وَرَسُولَهُ إِنَّمَا يُرِيدُ اللَّهُ لِيُذْهِبَ عَنكُمُ الرِّجْسَ أَهْلَ الْبَيْتِ وَيُطَهِّرَكُمْ تَطْهِيرًا﴾

“በቤቶቻችሁም ውስጥ እርጉ። እንደ ፊተኛይቱ መሃይምነት ጊዜ መገለጥም በማጌጥ አትገለጡ። ሶላትንም በደንቡ ስገዱ። ዘካንም ስጡ። አላህንና መልክተኛውንም ታዘዙ። የነቢዩ ቤተሰቦች ሆይ! አላህ የሚሻው ከእናንተ ላይ እርክሰትን ሊያስወግድና ማጥራትም ሊያጠራችሁ ብቻ ነው።” (አል’አህዛብ፡ 33)

**የተከበርሽ እህቴ ሆይ!** ይህ አጠቃላይ ሴቶችን በተለየ ሁኔታ የሚመለከት ሰላም የሚሰጥ ልቅናዋን ጠባቂ ተደርጎ የሚቆጠር ቁርኣንን እና ሐዲስን መሰረት ያደረገ ህግና ደንብ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ሙስሊም ሴት ክብሯ የሚጠበቅበት ፤ ከአደጋ እራሷን የምትከላከልበት ፤ እድለኛ የምትሆንበትን ታላላቅ አቅጣጫዎችን በመስጠት አላህ ታላቅ ጸጋ የዋለ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

**የተከበርሽ እህቴ ሆይ!** ፡ ሙስሊም ሴቶችን በከፍተኛ ሁኔታ ኢስላም አልቋል፡፡ ለተከበረ ህይዎቷ መስተካከል ዋስትና ወስዷል ፤ መለያዋን ሂጃብ አድርጓል ፤ ሴት ልጅ የአላህን ዲን አጥብቃ እስከያዘች ፤ የጌታዋን ትእዛዝ እስከጠበቀች ፤ መልእክተኛዋን ﷺ እስከታዘዘች ፤ ለሸሪዓው የተናነሰች እስከሆነች ድረስ ተከብራ ትኖራለች፡፡ በዱንያም ይሁን በአኼራ ታላቅ የሆነ ምንዳ ታገኛለች ፡፡

**የተከበርሽው እህቴ ሆይ!** ኢብን ሂባን የዘገበውን አቡሁረይራ رضي الله عنه ያስተላለፉትን ታላቅ ሐዲስ አስተውይ ፡-

"إذا صلت المرأة خمسها ، وصامت شهرها ، وحصنت فرجها ، وأطاعت بعلها ، دخلت من أي أبواب الجنة شاءت"

“ሴት ልጅ አምስት ወቅት ሶላት ከሰገደች ፤ ወሯን (ረመዷንን) ከጾመች ፤ ብልቷን ከጠበቀች ፤ ባሏን ከታዘዘች ፤ በፈለገችው የጀነት በሮች ትገባለች።” *(ኢብኑ ሂባን፡ 4163, ጦበራኒይ “አል’ሙዕጀም አል’ወሰጥ፡ 4598” ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል “ሶሂህ አት’ተርጊብ፡ 1931”)*

وروى الإمام أحمد من حديث عبد الرحمن بن عوف رضي الله عنه أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: "إذا صلت المرأة خمسها وصامت شهرها وحفظت فرجها وأطاعت زوجها قيل لها ادخلي الجنة من أي أبواب الجنة شئت"

“ሴት ልጅ አምስት ወቅት ሶላት ከሰገደች ፤ ወሯን (ረመዷንን) ከጾመች ፤ ብልቷን ከጠበቀች ፤ ባሏን ከታዘዘች ፤ በፈለገችው የጀነት በሮች ትገባለች።” *(አህመድ፡ 1661, ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል “ሶሂህ አት’ተርጊብ፡ 1932”)*

ከመጥፎ ተጧሪዎች እርቃ በእነዚህ ታላላቅ ነብያዊ ምክሮች ተጠቃሚ በመሆንና ህይዎቷን በመምራት እድለኛ የሆነች ሴት እንኳን ደስ አላት !

**ሙስሊሟ እህቴ ሆይ!** በዚህ ዘመን የኢስላም ጠላቶች ሂጃብሽን አስወልቀው ከተራ ዱርየዎች ተርታ ሊያሰልፉሽ ተዘጋጅተዋል። ለዚህ ተንኮላቸው ደግሞ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት ቴሌቪዥኖች፣ ሞባይሎች ፣ ጋዜጦች እና የተለያዩ ሚዲያዎች ናቸው። በመሆኑም አንዲት ሙስሊም ሴት አላህ ባዘዛት መሰረት ቀጥ ካለችና ሒጃቧን ባግባቡ ከለበሰች በኢማኗ ጥንካሬ የሚከሰቱ ውዝንብሮችን እና የሰይጣን ተንኮሎችን በአላህ ፈቃድ ትከላከላለች።

ከዚህ ቦታ የኡሙ ሰለማን ﵂ ጠንካራ ባህሪ ማስተዋል ይቻላል። ረሡል ﷺ ልብሱን በኩራት እየጎተተ ስለሚሄድ ወንድ ስለሚያጋጥመው ቅጣት በተናገሩ ጊዜ ኡሙ ሰለማ ﵂ ሴቶች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስትጠይቅ “አንዱ ስንዝር ታስረዝም” አሏት *“እንደዛ ከሆንማ እግሮቻችን ይገለጣሉ”* አለቻቸው። “በቃ አንዱ ክንዱ ታስረዝም ከዚህ በላይ አንዳትጨምር” በማለት ምላሽ ሰጡ። *(አህመድ፡ 4489, ቲርሚዚይ፡ 1731, ነሳኢይ፡ 5336)*

**ኢማኗ የደከመባት ሴት በተቃራኒው አንድ ስንዝር ወይም አንድ ክንድ ወይም ከዚያ በላይ እንደ ኢማኗ ድክመት አካሏን ትገልጣለች።**

ለቅኑ ጎዳና እንዲመራሽ ፤ ግልጽም ከሆነ ስውር ፈተና እንዲጠብቅሽ ፤ እርሱን በመታዘዝ ላይ እንዲያግዝሽ ፤ በሐቁ ላይ እንዲያጸናሽ አላህን እማጸናለሁ። እነሆ አላህ ዱዓን ሰሚና ተቀባይ ነውና ።

وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله وصحبه وسلم

# حجابك أيتها المسلمة

# መሙስሊሟ ሴት ሆይ! ሒጃብሽን አደራ!

إعداد:
الشيخ عبدالرزاق بن عبدالمحسن البدر

ትርጉም፡ ዩሱፍ አሕመድ

ባህር ዳር በሚገኙ የአህለሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሓዶራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን የቴሌግራም ሊንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ

http://t.me/alateriqilhaq